MINISTRY OF LABOUR

# በኳታር ስራ ለመቀየር አሰራሩ ምንድ ነው?

በኳታር የሚገኙ ሰራተኞች ካለ ምንም ተቃውሞ ሰርቲፊኬት(No Objection Certificate /NOC/)ሁሉም ስራዎች መቀየር ይቻላል።

ከታች የቀረቡ አሰራሮች በሰራተኛ ህግ ቁጥር 14፣2004 ስር የተካተቱ የቤት ሰራተኞች፣ የግብርናና የከብት እርባታ እንዲሁም አሳ አጥማጆችን ያካትታል። አሰሪዎችን ለመቀየር የሚከተሉትን ተግበራት መከናወን አለባቸው።

## 1 .ሰራተኛው ስራን ለመቀየር በሰራተኛ ሚኒስቴርኤሌክትሮኒክ ሲስተም (electronic system of the Ministry of Labour (MoL) ማመልከት አለበት:

- ሰራተኛው የሰራተኛ ለውጥ("Change Employer") ቅጽ ፕሪንት ማድረግ፣ መሙላት እና መፈረም አለበት። አዲሱ አሰሪ ፊርማውን ማኖርና የካምፓኒው ይፋዊ ማህተም በቅጹ ማኖር አለበት። ሰራተኛው ስራው ወደ የግል ቤተሰብ በሚቀይርበት ወቅት የአዲሱ አሰሪ ፊርማ በቂ ይሆናል።
- ሰራተኘው የኳታር መለያ((QID) ) እና የስልክ ቁጥር በማስገበት ወደ MoL ኤሌክትሮኒክ ሲስተም ከገባ በኃላ ፊርማ ያረፈበት ቅጽ ቅጂ ይጫኑ። የሞባይል ስልክ ቁጥር ከሰራተኛው QID መተሳሰር አለበት።

## 2 ማምልከቻውን ገቢ ከሆነ በኃላ EC(የአሰሪ ለውጥ) ቁትር በስክሪኑ ላይ ይታያል። ይህ ቁጥር ማመልከቻውን በትክክል መግባቱን ያረጋግጣል።

- .ሰራሕተኛታት የ EC ቁጥር መዝግበው መያዝ አለባቸው።
- በማንኛውንም ጊዜ ወደ ሚኒስቴሩ ድረገ(Ministry's website) ገብተው QID እና EC ቁጥር በመጠቀም ማመልከቻቸውን ያለበት ደረጃ ማወቅ አለባቸው።
- ሰራተኞች ጥያቄውን ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት በማንኛውንም ጊዜ በ MoL ኤሌክትሮኒክ ሲስተም ገብተው መሰረዝ ይችላሉ።
- ሰራተኞች አዲስ የስራ ውላቸው ማረጋገጫ እስካላገኘ ድረስ የጽሁፍ ጥያቄ ወደ MoL አቅርበው ማረጋገጫ ሲያገኙ ማምልከቻቸውን ማሰረዝ ይችላሉ። ፊርማቸውን ያረፈበት በአረብኛ የተጻፈ ደብዳቤ ወደ የስራ ግንኙነት ክፍል ማስገባት አለባቸው። በዚህ ደብዳቤ ለምን ለማሰረዝ እንደሚጠይቁ በአጭሩ በመግለጽ ሲያመልክቱ የተሰጥዎትን የEC ቁጥር፣ የ QID ቅጂን የሞባይል ስልክ ቁጥርን አካተው ማቀረብ አለብዎት።

## 3 ሰራተኞች ማምልከቻቸውን ውድቅ የሚደረግበት ሁኔታ ሊያጋጥም ይችላል፤ ለምሳሌ ሰራተኞች ቅጹን በትክክል ካልሞሉት ወይ አዲሱ አሰሪ አዲስ ሰራተኞች ከመቅጠር የተከለከለ ከሆነ።

## 4 የማመልከቻው ሂደት ከተጀመረ በሃላ፤ ሰራተኛው የስራ ለውጥና የማሳወቅያ ጊዜ የሚያረጋግጥ አጭር የጽሑፍ መልዕክት( SMS) ከሚኒስትሪው ይደርሰዋል።

በዚህ ወቅት ነው የቀድሞ እና የአሁኑ አሰሪዎች እንዲያውቁ የሚደረገው።

- .ሰራተኛው አሁን ላለው አሰሪ 2 ዓመት ወይም ያነሰ ከሰራ የማሳወቅያ ጊዜው1 ወር ይሆናል።
- ሰራተኛው ከ2 ዓመት በላይ ከሰራ የማሳወቅያጊዜው2 ወር ይሆናል።
- የማስተዋቅያ መጨረሻ ጊዜ በሚኒስቴሩ በአጭር የጽሁፍ መልዕክቱ ተመላክቷል።
- ሰራተኛውን እና የአሁኑ አሰሪ ካልተስማሙ በስተቀር ሰራተኛው በማስተዋቅያ ጊዜው ወቅት ከአሁኑ አሰሪው መስራት መቀጠል አለበት።

## 5 የማሳወቅያ ጊዜው ሲጠናቀቅ አዲሱ አሰሪ በ MoL ዲጂታል አውቶንኬሽን ለዘርፈ ብዙ-የቋንቋ ስራ ውል(Digital Authentication System for a Multi-lingual Employment Contract) በኩል የስራ ውል ለማድረግ ይዘጋጃል።

ይህ ከማስተዋቅያ ጊዜው በተጠናቀቀ በሶስት ወራት ይጠናቀቃል። ሁሉም መረጃ በሚሞላበት ወቅት አዲሱ አሰሪ የስራ ውሉን ፕሪንት በማድረግ የሰራተኛውንና የአዲሱ አሰሪ ፊርማ እንዲያርፍበት ይደረጋል። ሰራተኛው በውሉ አንቀጾች ሲስማማ ፊርማውን ማኖር ይችላል።

- አዲሱ አሰሪ የተፈረመበት ውል ይረጋገጥ ዘንድ በሚኒስቴሩ ድረገጽ ይጫነዋል።
- በማጠቃልያ አዲሱ የተረጋገጠ የስራ ውል ቅጂ ለሰራተኛው ይሰጠዋል።

## 6 የስራ ውል ከተረጋገጠ በኃላ አዲሱ አሰሪ ለሰራተኛው የሚሆን QID እንዲሰጠው ለአገር ውስጥ ሚኒስቴር ይጠይቃል።

## 7 አሁን ሰራተኛው ስራውን መጀመር ይችላል

ሰራተኛው ከአሰሪው አዲስ QID(ከክፍያ ነጻ) ያገኛል።

### ማስተዋሻ

ሰራተኞች እና አሰሪዎች ሁሉ ጊዜ የስራ ውል ቅጂ ከMoLፖርታል (Mol portalማውረድ ይችላሉ።

### ጠቃሚ ሊንከች

Submit your application to change jobs

Check the status of your employer change application

Submit a labour-related complaint to MoL

### ተጨማሪ መረጃ ከየት አገኛለሁ?

ለበለጠ መረጃ የሰራተኛ ሚኒስቴር በሆትላይን በ**40288101**፤ ኢመይል info@mol.gov.qa ድረ ገጽ www.mol.gov.qa ወይመ ጽህፈት ቤታችንን ይጎብኙ።